# *የታሪክ ትርፍ ኣንጀት!*

## *ከዓሣዬ*

*ኧረ ታገሥ በሉት!*
*ተው ተጠንቀቅ በሉት!*
*ይኸን ቀባጣሪ የምላሥ ጠረኛ*
*በሥየል ትርፍ ኣምራች የባዕድ ቅጥረኛ*
*የታሪክ ትርፍ ኣንጀት ኣፍቃሪ ዘረኛ ፡*
*ምን ይሉኝን ኣያውቅ ውሸቱ ኣያልቅበት*
*ከኣገሩ እርቆ የምላሥ ጠር ሲያዘምት ።*

*የውሸቱን ቋጠሮ ደምሮና ኣባዝቶ*
*ሦስት መቶ ሺህ ጠሩን በወያኔ ኣዝምቶ*
*በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ድልን ተቀዳጅቶ*
*ነፃ ኣገር ሊያወጣ ምርኮኛውንም ፈትቶ*
*ይኸ ብርር ኣምላኩ፡*
*ኪሥ ኣውላቂ ጠሩን ሙዳይ ኣሸክሞ*
*ሰደድ እሣት ለቋል ታማኙን መልምሎ ።*

*ላም ኣለኝ በሰማይ ይሄ የህልም ቅቤ ኣንጓች!*
*ውሸት ቆርጦ ቀጣይ የምኞት ጠር ኣዝማች!*
*ከሃቅ ጋር ተጣልቶ ቢሆንም ልበ ቢስ*
*እሥቲ እንሥጠው ሣንባ!*
*የታሪክ ቀላ ቁሰል፡የታሪክ ትርፍ ኣንጀት ሆኖ ከሚወገዝ*
*በመሥፍን የጠላሁት ከቶም በእሱ እንዳይደርሥ*
*እንደው ለለውጥ ያህል ውሸቱን ቀናንሶ ሃቅን በመተንፈሥ!*
*ደግሞም ትግሉን ቢያጠብቅ ለትርፍ ከመልከሰከሥ!!!*

*AUG /15/2014 GC*